


# አጭር ማስታወሻ በሙሴ መጻሕፍት ዙሪያ



## የራስጌ ማስታወሻ በሙሴ መጻሕፍት ዙሪያ

† የሙሴ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ አምስት መጻሕፍት ናቸዉ።

- አምስቱ የሙሴ የህግ መጻሕፍት ፥
- አምስቱ ኦሪቶች፥
- The First five books of the bible፥ እና
- The Pentateuch ይባላሉ።

† አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት በቅደም ተከተል፤

- ኦርት ዘፍጥረት፥
- ኦሪት ዘፀአት፥
- ኦሪት ዘኍልቍ
- ኦሪት ዘሌዋዉያን፥ እና
- ኦሪት ዘዳግም ናቸው።





† ኦሪት ማለት ህግ፥ ትዕዛዝ፥ ፍትህም ማለት ሲሆን፤ ዘፍጥረት ደግሞ በግዕዝ ፍጥረት ማለት ስለሆነ፤

† ለምሳሌ፡-ኦሪት ዘፍጥረት ስንል የፍጥረት ህግ ፥ የአፈጣጠር ሥርዓት ወይም የፍጥረት ስርዓት ማለታችን ነው፡፡

- ➢የነገሮችን ሁሉ አጀማመር በዋናነት የሚተርክ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነውና፡፡
- ➢ስሙም የተወሰደው በመጽሐፉ ወደ 11 ጊዜ ልደት ወይም ትውልድ እያለ የደጋገመውን በመያዝ ነው፡፡





† የዘፍጥረት መጽሐፍ በቴዎሎጂ (Teology) በጣም ሀብታሙ መጽሐፍ ነው፡፡

"The root of all Subsequent revelations are planted deep in genesis, and whoever would truly comprehend that revelation must begin here."

[J.S. Baxter]

"We have in germ form, almost all of the great doctrines which are afterwards fully developed in the books of scriptures which follow."

[A.W.Pink]

† በአሪት ዘፍጥረት ላይ በዋናነት የሚከተሉት ተገልጠዋል፥

- እግዚአብሔር ራሱ በራሱ ህላዊ ያለው፥ ብርቱና ኃያልም ፈጣሪ፥ ጌታ፥ ገዥ እና የቃል ኪዳን አምላክ (the covenant God) ሆኖ ተገልጧል፡፡ በዚህም ያህዌ፥ ኤሎሄም እና አዶናይ በሚሉት ዋነኛ ስሞቹ እንደተጠራባቸዉ፥
- የስላሴ አስተምሮም የመጀመሪያ ፍንጮች ($1^{26}$,$11^{7}$,$18^{1-9}$)፥
- የሰይጣን ተንኮል፥





† በአሪት ዘፍጥረት ላይ በዋናነት የሚከተሉት ተገልጠዋል፥

- የወደቀው ሰው ባህርይ፥
- የእግዚአብሔር መለኮታዊ ምርጫና የማዳን ፀጋው፥
- በእምነት ብቻ መጽደቅና የድነት ዋስትና ፅንሰ ሃሳቦች፥
- የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ የሚያሳየዉ የሄኖክ መነጠቅ፥





† በአሪት ዘፍጥረት ላይ በዋናነት የሚከተሉት ተገልጠዋል፥

- የፀሎት ኃይል እና የቅድስና አስፈላጊነት፥
- የእግዚአብሔርን ኃጢአት ቀጭነት፥
- በብዙ መንገድ የተገለጠ የአዳኙ መሲህ መምጣት፥ መሞት፥ መነሳት እና ዘላለማዊ ሊቀ ካህንነቱ፥ እና
- ከእግዚአብሔር በቀር የሁሉም ነገሮች መጀመሪያ በዚህ መፅሐፍ ተገልጠዋል፡፡





† ከእግዚአብሔር በቀር፤ ከተገለጡት መጀመሪያ ነገሮች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፤ የዓለም ፥ የሕይወት፥ የሰው፥ የሰባት ቀን ሳምንት፥ የጋብቻ፥ የቤተሰብ፥ የኃጢአት፥ የመስዋዕት፥ የድነት ፥ የሞት፥ የሀገር፥ የከተማ፥ የሙዚቃ፥ የጹሑፍ ፥ የአርት፥የእርሻ፥ የቋንቋ ወዘተ መጀመሪያዎች

ሙሉውን የዘፍጥረት መጽሐፍ እንደተፃፈው፣ (በጊዜና በቦታ የተደረገ) የተከናወነ ታሪካዊ ክስተት እንደሆነ አድርጎ መቀበል፤ ለክርስትና እምነት ልክ የጌታን ትንሣኤ ታሪካዊ ክስተተ አድርጎ መቀበል አስፈላጊ እንደሆነው ነው፡፡



...ትንሣኤዉ እዛ የተገባዉ ተስፋ ፍጻሜ ነዉና!!!





† ለዚሁ ነዉ ጌታና የተቀሩት ሀዋሪያቱ በተለይየመጀመሪያውን የዘፍጥረት ክፍል ታሪካዊነቱን በመቀበል ጠቅሰው ያስተማሩት፣ ጠቅሰዉ የጻፉትም፤ ለምሳሌ

- ጌታ፡- ስለ መፋታት [ማቴ19 4-8]፥ ስለ ሥነ-ፍጥረት [ማር13 19]፤
- ጳውሎስ፡-አዳም እና ሔዋን የተፈጠሩ ሰዎች እንደነበሩ [1ጢሞ2 13-14፣ሮሜ 5 12-14፣2ቆሮ11 3]፤
- ጴጥሮስ፡-ስለ ጥፋት ውሃ [1ጴጥ3 20]፤
- ይሁዳ፡-ስለ ሔኖክ [ቁ.15] እና
- ዮሃንስም በራእዩ፡-ስለ ቀደመው እባብ፥ ስለ ገነትም ወዘተ ጠቅሰዋል።





†የዘፍጥረት መጽሓፍትን ፅንሰ ሃሣብ መረዳት፤ ጠቅላላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሣብ የምንረዳበት መሠረት ነዉ። በተለይም የመጀመሪያዎች 12 ምዕራፎች ደግሞ እጅግ መተኪያ የሌላቸው እንደሆኑ እናያለን፡፡







የመጽሐፉ አከፋፈል፤

† By G.Campbell Morgan፡

- Generation (Chapter 1-2, Creation)
- Degeneration (Chapter 3-11, the Fall)
- Regeneration (Chapter 12-50፣via Abraham and His descendents)

† በብዙ መጽሓፍ ቅዱስ አስተማሪዎች፤

ሀ. ከአዳም እስከ አብርሃም ፡- የሰው ዘር ታሪክ

- ሥነ-ፍጥረት (ምዕ.1-2)
- ውድቀት (ምዕ. 3)
- የጥፋት ውሃ ፍርድ (ምዕ. 4-9)
- የባቢሎን ቅጥረ ፍርድ (ምዕ. 10-11)

# የመጽሐፉ አከፋፈል፤

ለ. ከአብርሃም እስከ ዮሴፍ፡- የተመረጠው ዘር ታሪክ

- አብርሃም (ምዕ. 12-24)
- ይስሃቅ (ምዕ. 25-26)
- ያዕቆብ (ምዕ. 27-36)
- ዮሴፍ (ምዕ. 37-50)

*መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።*